# የዶክተሩ የፖለቲካ ውስልተና



አቶ ሞላ አስግዶም ከትግራይ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ መሪነቱን በፍቃዳቸው ለቀው፣ ከጥቂት የንቅናቄው አባላት ጋር ወደ ወያኔ ጎራ መኮብለላቸውን አስመልክቶ የሰሞኑ ዜና ሆኖ ከርሟል፤ ይህም ሆኖ የአሜሪካ ድምጽ VOA የአማርኛው ቋንቋ አገልግሎት የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር [ሕውሓት ] መስራችና አቀንቃኝ ለሆኑት ለዶክተር አረጋዊ በርሄ ቃለመጥይቅ አቅርቦላቸዋል፤ ከቀረቡላቸው መጥይቆች ውስጥ በሦስቱ ላይ መተችት እወዳለሁ፤ በኤርትራ መሽጎ ስላለው የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ ፣ አርበኞች ግንቦት ሰባት፣ ሰለ አቶ ሞላ አስጎዶም በሰጠው መግለጫ፣ የአቶ ሞላ አስግዶም መክዳት ለኤርትራ መንግሥት ሽንፍት መሆኑን መጠቆማቸው ላይ እሄድበታለሁ፤ በመጀመሪያ 'የዶክተሩ ፖለቲካ ውስልትና ' የዶክተር አረጋዊ በርሄን የፖለቲካ አካሄድ ለማሳየት እንጂ ስዕብናቸውን ለመዳፈር አይደለም፤ ምንም እንኳን ዶክተሩ የዘውግ ፖለቲካ አራማጅ ቢሆኑም ከዘር በፊት ሰው በመሆናቸው ሁለታችንም የአምላክ ፍጡራን ነን ብዬ አምናለሁ፤ ውስልትናው የሚከሰተው ግን እንደሰው ማሰብ አቁመን እንደዘር ስናስብ፣ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ አቀራረብ መኖር የለበትም ባይ ነኝ። ለምሳሌ በኤርትራ መሽጎ ያለው የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ ለአስራ አራት ዓመት በኤርትራ ቆይታው ይህ ነው የሚባል ጥቃት በወያኔ ላይ አለማድረሱን የደረሱበት በእርሳቸው መረጃ ሊሆን ስለሚችል ማስተባበያ የለኝም፤ የንቅናቄው አባላት ቁጥር መጨመሩን ላይ እስማማለሁ፤ ያም ሆኖ ግን ሀገሩን የለቀቀበትን ዋነኛውን ምክንያት ዘለውታል፤ ውስልትናው እዚያ ላይ ነው። በእርሳቸው ሊቀመበርነት በደደቢት ዋሻ 1968 ዓ ም የነደፉት የዘር ሰነድ ወይም ማንፌቶ ዘንግተውት ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይዘነጋውም፤ የዚያን ገፈት እየተጋተው ነው፤ የሙቶ ዓመቱን በዘውግ እየተካፋፈልን እንድንናኮር የቤት ሥራ የሰጡን ፕሬዘዳንት ኢሲያስ አፈወርቂ ሳይሆኑ ዶክተር አረጋዊ በርሄና አቶ ሰባት ነጋ መሆናቸውን በገቢር እያየነው ነው። ለመጥቀስ ያህል፣ የአሲባ ፍቅር በካሕሳይ አብረሃ አስረስ 2005 ዓም ገጽ 180፤ አረጋዊ በርሄ የምትባለው፣ 'የትግራይን ሕዝብ እያደናገርክ መኖር የለመድክ፣ ለምንድነው? ሐቀኛ ለመምሰል የምትሞክረው እ? በትግራይ ሕዝብ ስም ለማደናገርና ለማጭበርበር ነው? 1968 ዓ ምህረትም እንደዛሬዎቹ የትገራይ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ ለነጻነት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት፣ ይታገሉ ከነበሩ የትግራይ ወጣቶችን ገድል የሚገልጽ ነው፤ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ይመሩት የነበረውን ሕውሓትን የዘወግ ፖለቲካ ይፋለሙ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች እንደነበሩ ያሣያል። ያም ሆኖ ያካባቢው ሕዝብ ሁለታችሁም ልጆቻችን ናችሁ ለምን አብራችሁ አትታገሉም በማለት ግፊቶችን እንደሚያደርጉ ደራሲው በመጻፉ ውስት ጠቅሷታል፣ የትግራይ ሕዝብ የዴሞክራቲክ ንቅንቄ ሊቀመበር የነበሩት አቶ ሞላ አስግዶም በትግራይ ስም ሥልጣን ላይ ያለውን ዘርኛ መንግሥት በቁርጥኝነት ለማስወገድ ለመነሣት ያላቸው የንቃት ሒሊና ብቃት ተፈታትኗቸው ለወያኔ እጅ ሰጥተዋል፤ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ያላደረጉትን ከመንደራቸው ያልወጡን ገበሬ አቶ ሞላ አስግዶምን ለነጻነት ለፍተህ ለዴሞክራሲ ለኩልነት ለአንድነት ጥምረቱን በምክትል ሊቀመበርነት ለምን አልመሩም በማለት መፍርድ ፍርደ ገምድልነት ነው። ቀደመውንም በወያኔ ሰላይነት ተመድበዋል ማለትና አንድ ለአምስት ጥፍነጋውን አጋኖ ማቀረባችውን ከዶክተር አርጋዊ በርሄ ጋር አልስማማም። ለስለላውም ለጥፍነጋውም አንዳንድ ምሳሌ ልስጥ፣ አቶ ሞላ እያሉ አቶ አንዳርጋቸውን ለመግደል ለምን ሽጉጥ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ ማሻገር አስፈለገ? ለጥንፈጋው መክሸፍ፣ የአይር ኃይላችንን መጥቀስ ይበቃል። ዶክተር አረጋዊ በረሄ ሀገር ጥለው በረሃ ሰለገቡት ወጣቶች ዋነኛውና መርዙ የሆነውን የዘወግ ፖለቲካ መሆኑን እያወቁ በፖለቲካ ውስልትና ቢያልፉትም ፣ የአሜሪካው ፕሬዘዳንት ባራካ ኦቦማ ሳይቀሩ በንግግራቸው የቱን ያህል የዘውግ ፖለቲካ ሀገርን እንደሚጎዳ ትውልድን እንደሚያጫጫ ጠቁመው ።

አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ አቶ ሞላ አስግዶምን አስመልክቶ ካቀረባቸው ሁለት ትንታኔዎች ለአንዱ ዶክተር አረጋዊ በርሄ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት በአማሪካው ድምጽ ጋዜጠኛ ጥያቄ አቅርቦላችው ነበር፤ ጥያቄው ይህ ይመስላል፤ 'ሁለት አፍራሽና ኋላ ቀር የፖለቲካ አዝማማዎች [trends] አሉ፤ ከነኝህ ውስጥ አንደኛው ራስን በፖለቲካ አመለካከት ዙሪያ ከማሰባሰብ ይልቅ በጎጥ፣ በዘወግ ደረጃ፣ የመመልከትና ሀገራዊ ፖለቲካን በደም ቆጠራ የመመዘን አባዜ ነው። ይህን አገላለጽ ለጊዜዊ ጥቅም ለማናፈስና አንዱን በሰንን ለማሰለፍ ብለው አልፈውታል፤

ዶክተር አረጋዊ በርሄ በተለመደው የፖለቲካ ውስልትና በሕዝቡ ውስጥ የዘር ፖለቲካ እንብዛም እንዳልተስፋፋ ሊያስተባብሉ ሞክረዋል፣ ለዚያም ጥቂት የሕውሓት አባላትና ሟቹ ጠቅላይ ሚንስተር መለስ ዜናዊ እንደሆኑ ሊያሳምኑንም ጥረዋል፣ እንግዲህ የወያኔን ጅንራሎችን ቁጥር እንደቡና ፍሬ ልንቆጥር ነው ፣ ያለበለዚያ ደግሞ እንደደይፋትና ጥሙጋ፣ የአርማጮ ገበሬ ወዳጅነት፣ የወለጋና የትግራይ ገበሬ እኩል በዘር ተጨቋኝነት አጋነን እንድናወሳ የፈለጉ ይመስላል፣ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ በኢትዮጵያ አየር ኃይልና በተለያዩ ተቋማት የሚፈጸመውን የዘር ልዩነት አላየንም አልሰማንም አንናገርም እንበል? እስር ቤቶች ኦሮመኛ ይናገራሉ የሚለውን ትግረኛም ይናገራሉ

እንበል? አማርኛ ተናጋሪው በሕግ ተቀርጾ የተዘመተበት ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ አልገባም። ለነገሩ የአርማጮ ገበሬ ለትግራይ ገበሬ አይቀርበው እሣ! ይህቺን የወሊጋና የትግራይን ማቀራረብ ጉዳይ አቶ አስራት ገብሩም በመድረክ ስብሰባ ላይ አንስቷታል፤' ሐቡይ ኩርኩር ሐቡይ ኩርኩር ትልቁ የአማራ ውሻ' የሚለውን ሽውዶ ለማለፍ ይሆን? በመልሳቸው አርበኞች የሚለው ቃል ገድፈው 'ግንቦት ሰባት ለጊዜዊ ጥቅምና አንዱን በጎኑ ለማሰለፍ ብለው አልፈውታል። ዶክተር አረጋዊ በርሄ የዘወግ ፖለቲካ ሠሪያና ፈጣሪ መሆናቸውን በሕይወት እያሉ ሳይነግሩን እንዳያልፉ እማጠናቸዋለሁ። ያም ሆኖ ግን ከአንዳንድ የስልጣን ጥመኞች ስብስብ ጡት ተጣብተው የሕብረ-ቤሔር ፖለቲካ አራማጅ ነኝ እንዳይሉን፤ ሐቁ ግን አሁንም የዘሩ ፖለቲካ እንደተጣባችው ፍትው አድርገው የሚያሳዩ ብዙ መረጃዎች አሉ። አንዱን ልጥቀስ፣ በሕይወት የሌለውን መለስ ዜናዊውን ብቻ የዘወግ ፖለቲካው አራማጅ አድርገው ሲያቀርቡ ባልደሮቦቻቸውን ሰባት ነጋንና አባይ ፀሐዬን ያልወነጀሏቸው በሕይወት ስላሉ ወይም ግንኙነታቸው እንዳሻክር ለመሆኑ ታምራት ገለታን ደጅ መጥናት አይሻም፡፡ በኦሮመኛ እንዲህ ይተረታል፣ 'ኬስኬሳ አዱሬን ብኔሣ! ' ውስጥ ውስጡን ድመትም አውሬ ነው።

ሌላውና የመጨረሻው አቶ ሞላ አስግዶም ትግሉን ከድተው ወደወያኔ በመግባታቸው በኤርትራ ላይ ሽነፈት እንደደረሰ አጋነው አቅርበዋል፤ ለዶክተር አረጋዊ በርሄ ሽነፈት የሚለው ቃል ፍቺ አይከብዳቸውም፤ ሻዐቢያ ፣ ወያኔን በዓለም አቀፍ ደረጃ መሣቂያ እንዳደረገው የሚያውቁ ይመስለኛል፤ ለምሳሌ በገለልተኛ ቡድን ባዲሜ ለኤርትራ መስጠቱን የዓለም ሕብረተሰብ እያወቀው በጭለማ ለሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የተነገረው ለእርሱ እንደተሰጠው ነበር፤ አሸባሪው ን አልሸባብን በሱማሊያ የሚቀሳቀሰውን ኤርትራ ታሰለጥናለች፣ ታስታጥቃለች በማለት ወያኔ ወንጅሎ ነበር፤ በዓለም መንግሥታት መርማሪ ተጣርቶ ወያኔ የጋገረው የውሸት ዳቦ መሆኑ ተረጋገጠ፤ የኦሮሞ የነጻነት ግንባር በኤርትራ ተልኮ አደጋ አደረሰ የሚለውን ዊኪ ሊክ አጋለጠ፤ ዝርዝሩ ይቀጥላል፤ ታዲያ አንድ ገበሬ ሞላ አስግዶም ወደ መንደሩ በመመለሱ ለኤርትራ ሽክም ቀለለለት እንጂ እንዴት ሽነፈት ሊሆን ይችላል ? እንዴትስ መግለጫ ከኤርትራ ይጠበታል? ዶክተር ራሷ ገለጸውታል፤ በአቶ ሞላ የሚመራው ት ህ ዴ ን ቀለብተኛ ምንም አይነት ተለኮ ያላከናወነና የተሰላቸ መሆኑን ገልጸዋል፤ ሰለዚህ ት ህ ዴ ንን የሚሰራ ድርጅት ለማደረግ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ የአማራው ሕዝብ ንቅናቄ እና የአፋር ሕዝብ ንቅንቄ 'ሀገር አድን ንቅንቄ ' በማለት ጥምረት መስረተዋል፤ ፕሮፌሰር ብረሃኑ ነጋ ሊቀመበር ሲሆኑ አቶ ሞላ አስግዶም በምክትል ሊቀመበርነት ተመርጠው ነበር፤ ትግሉ የሚጠይቀውን ተግዳራት ለመቋቋም ከጅምሩ ሰለ አሰጋቸው አቋርጠው ሄደዋል፣ ሰለዚህ ለኤርትራ ሽነፈቱ ምኑ ላይ ነው? በኢሳት ሰለ የአፍሪካ ቀንድ ኮንፍራስ ላይ ለሰተገኙት ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ ከሰጡት ትችት አንዷት ሰንኝ ልዋስ፤ በውጭ ሀገር ማንኪያና ሹካ መያዝ ያቃታቸው መሬት ወርደው ለውጥ በኢትዮጵያ ሊያመጡ ያልቻሉ በዋሽግተን ዲሲ ይሰባሰባሉ ብለው ነበር። መሬት ላይ የወረዱትን ፕሮፌሰር ብረሃኑ ነጋ ሰለ አቶ ሞላ አስግዶምን አስመልክቶ የሰጡንን መግለጫ ለጊዜው እንቀበለው። አጀኳ ዶክተር! አርጋዊ በርሄ ! የዘውግና የክልል ፖለቲካ ግባ ከመሬቱ ይፍጸማል።

ታደለ መኩሪያ

tadele@shaw.ca